# የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1026/2017

Oil-seeds and Grain Products Direct Marketing System Directive No. 1026/2017

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry of Trade and Regional Integration

መስከረም 29፥ 2017

# መመሪያ ቁጥር 1026/2017

# የቅባት እህሎችን እና የጥራጥሬ ምርቶችን የቀጥታ ግብይት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

# የቅባት እህሎችን እና የጥራጥሬ ምርቶችን የቀጥታ ግብይት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 22 (1) መሠረት የሀገር ውስጥና የውጪ ንግድን የማስፋፋት ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፤

ይህን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ዘርፍ የገቢ ግኝት በላቀ ደረጃ ለማሳደግ ግብይቱ ለህገ ወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድ ያልተጋለጠ፣ የተሳለጠ፤ ጊዜ ቆጣቢ እና የግብይት ሎጅስቲክስ ወጪን የቀነሰ እና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል አማራጭ የግብይት ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 (4) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"የቀጥታ ግብይት ሥርዓት"** ማለት ሻጭ በሆነ አቅራቢ እና ገዥ በሆነ ላኪ መካከል በቀጥታ ግብይት ትስስር የሚካሄድ የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት ስርዓት ነው፤

2/ **"የቅባት እህሎች"** ማለት ኑግ፣ ተልባ፣ ሱፍ፣ ለዉዝ፣ የዱባ ፍሬ፣ ጉሎ፣ ሰሊጥ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፤

3/ **"የጥራጥሬ ምርቶች"** ማለት ነጭ ቦሎቄን ጨምሮ የተለያዩ የቦሎቄ ዝርያዎች፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር፣ ምስር፣ ባቄላ፣ ሽምብራ፣ አተር፣ ጓያ፣ የእርግብ አተር፣ ግብጦ እና የመሳሰሉት ናቸው፤

4/ **"ምርት"** ማለት የቅባት እህል ወይም የጥራጥሬ ምርት ነው፤

5/ **"የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል"** ማለት ለቅባት ዕህሎች እና ለጥራጥሬ ምርቶች መገበያያነት እንዲሆን ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የክልል አካል የተከለለ ስፍራ ነው፤

6/ **"አቅራቢ"** ማለት ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል የገዛቸውን የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች በቀጥታ ለላኪ አቅርቦ የሚሸጥ ነጋዴ ነው፤

7/ **“ላኪ”** ማለት ከአቅራቢ የገዛቸውን የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ለወጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነዉ፤

8/ **“የማዘጋጃ ኢንዱስትሪ”** ማለት የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን አበጥሮና ከባዕድ ነገር አፅድቶ ለገበያ ለማቅረብ የማሰናዳት አገልግሎት የሚሰጥ ማእከል ነው፤

9/ **“የምርት ዘመን”** ማለት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ ኅዳር 1 ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት 30 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤

10/ **“ሚኒስቴር”** ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

**11/ “የበላይ ኃላፊ”** ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ሲሆን ለዚህ መመሪያ ዓላማ የወጪ ንግድ ዘርፍን የሚመራ ሚኒስትር ዴኤታን ይጨምራል፤

12/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

13/ **“ሰው”** **ማለት** ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

14/ በዚህ መመሪያ **በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም** ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በቅባት እህሎች እና በጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ስርዓት እና በግብይቱ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የቀጥታ ግብይት የአሰራር ስርዓት</u>

## 4. <u>የቀጥታ ግብይት ትስስር ስለመፍጠር</u>

1/ በቅባት እህሎች ወይም በጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ትስስር የሚፈጠረው በአንድ አቅራቢ እና በአንድ ላኪ መካከል ከአንድ የምርት ዘመን ላልበለጠ ወይም ቢያንስ ከሦስት ወራት ላላነሰ ጊዜ የሚቆይ ሥልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ ውል ሲኖር እና ውሉ ለሚኒስቴሩ ቀርቦ የተመዘገበ ሲሆን ነው፡፡

2/ በአቅራቢ እና በላኪ መካከል የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በድርድር ላይ ተመሥርቶ የሚካሄድ ሆኖ የዋጋ ስምምነት ላይ የሚደረሰዉ የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረገው የቀጥታ ግብይት ትስስር ውል ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

ሀ) የአቅራቢውን እና የላኪውን ሙሉ ስም እና አድራሻ፤

ለ) ግብይት የሚፈጸምበትን የምርት አይነትና መጠን፤

ሐ) ዋጋ፤

መ) የመረካከቢያ ቦታ፡፡

5. <u>ስለ ርክክብ</u>

1/ በቀጥታ የግብይት ሥርዓት የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ርክክብ የሚካሄደው ምርቱ በሚመዘንበት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ርክክብ ማዕከል፣ በማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም በማከማቻ መጋዘን ይሆናል፡፡

2/ አቅራቢና ላኪ ግብይት የተፈጸመበትን የምርት አይነት እና መጠን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ርክክብ ማዕከል በማቅረብና ምዝና በማካሄድ የምዝና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

6. <u>ስለ ክፍያ አፈጻጸም</u>

ላኪው ለተረከበው የቅባት እህል ወይም የጥራጥሬ ምርት የክፍያዉን አላማ በመግለፅ ርክክብ በተፈጸመ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቅራቢው ሙሉ ክፍያ በባንክ በኩል በአንድ ጊዜ መፈጸም እና የባንክ የክፍያ ደረሰኝ መያዝ ይኖርበታል፡፡

7. <u>የአቅራቢ ግዴታ</u>

በቀጥታ ግብይት የሚሳተፍ ማንኛውም አቅራቢ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማእከል የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ግዥ ከፈጸመ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ ለላኪ ሽያጭ በመፈጸም የማስረከብ፤

2/ የቀጥታ ግብይት ትስስር ለገባለት ላኪ ግዴታዉን ሳይወጣ ለሌላ ገዥ ሽያጭ ያለመፈጸም፤

3/ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ርክክብ ማእከል ወስዶ ለማስመዘን ወይም የተመዘነ ምርት ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም ወደ ማከማቻ መጋዘን ለማድረስ ተገቢውን የመሸኛ ሰነድ የመያዝ እና የማጓጓዝ፤ በተቆጣጣሪአካላት ሲጠየቅም የማሳየት፤

4/ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን  ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ አቅርቦ ሳያስመዝን ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም ወደ ማከማቻ መጋዘን ያለማጓጓዝና ያለማከማቸት፤

5// የአንድን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የአንድን የምርት ዘመን ከሌላ  የምርት ዘመን እና የመኸር ምርትን ከበልግ ምርት ጋር ሳይቀላቅል እንደ ምርቶቹ ባህሪ የምርትን ዱካ በጠበቀ መልኩ የማጓጓዝ፣ የማስመዘን እና የማስረከብ፡፡

8. <u>የላኪ ግዴታ</u>

ማንኛውም በቀጥታ ግብይት የሚሳተፍ ላኪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ የምርት ዘመኑን የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የወጪ ንግድ እቅድ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ የማቅረብና ሲጸድቅም በሥራ ላይ የማዋል፤

2/ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ከተፈጸመበት አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የርክክብ ማእከል፣ ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም ወደ ማከማቻ መጋዘን

ለማድረስ አስፈላጊውን የመሸኛ ሰነድ በመያዝ የማጓጓዝ፤ በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማሳየት፤

3/ ግብይት የፈጸመባቸውን የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የርክክብ ማእከል አቅርቦ የማስመዘን እና የምዘና መረጃ ሰነድ የመያዝ፤

4/ የክፍያውን አላማ በመግለጽ በባንክ በኩል ለአቅራቢዉ ክፍያ የመፈጸም እና የባንክ የክፍያ ሰነድ የመያዝ፤

5/ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተሰጠውን የምርት መጠን የምዘና መረጃ እና ለአቅራቢ ክፍያ የፈጸመበትን የባንክ ደረሰኝ በማቅረብ ከሚኒስቴሩ የኮንትራት ምዝገባ እና የኤክስፖርት የመላኪያ ፈቃድ የማግኘት፤

6/ ግብይት የፈጸመባቸው የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች መጠን አንድ ኮንቴነር ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያን የምርት ጥራት ደረጃ እና የገዢዉን ፍላጎት በማሟላት አዘጋጅቶ ለውጭ ገበያ የመሸጥ፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለዉጭ ገበያ ሽያጭ መፈጸም ካልቻለ ለሚኒስቴሩ የበላይ ሃላፊ በጽሁፍ በማመልከት አሳማኝ ሆኖ ሲገኝ ከሁለት ወራት ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት የመጠየቅ፤

8/ በቀጥታ የግብይት ሥርዓት የገዛቸውን የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች በአንድ የምርት ዘመን ውስጥ ወይም ካልተቻለ አንድ የምርት ዘመን ባለቀ 60 ቀናት ውስጥ አጠናቆ ለውጭ ገበያ የመላክ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

### 9. ስለማጓጓዝ

ማንኛውም የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪ፡-

1/ ምርቱን ለሌላ አገልግሎት ጥቅም ላይ ባልዋለ እና ለዚሁ አገልግሎት ብቻ በተዘጋጀ የመያዣያ ከረጢት ማጓጓዝ አለበት፡፡

2/ የምርቱን ጥራት ከሚያበላሹ እንደ ኬሚካል፣ ነዳጅ፣ ፈሳሽ እና ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ጋር ሳይቀላቅል ምርቱን ማጓጓዝ አለበት፡፡

3/ ምርቱን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የማከማቻ መጋዘን ሲያጓጉዝ ተገቢውን የመሸኛ ሰነድ መያዝ አለበት፡፡

### 10. ስለ አዘገጃጀት

ማንኛውም የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የማዘጋጀት አገልግሎት ሰጪ፡-

1/ ምርቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተመዘነ ምርት መሆኑን በማረጋገጥ መረከብ አለበት፡፡

2/ የምርቱን የጥራት ደረጃ በጠበቀ ሁኔታ ማዘጋጀት አለበት፡፡

3/ ምርቱን ከተፈጥሮ ባህሪው ጋር ከማይስማሙ፣ ከሚጻረሩ ወይም ይዘቱን ከሚቀይሩ ከማንኛዉም ባዕድ ነገሮች በጸዳ መልኩ ማዘጋጀት አለበት፡፡

4/ በዝግጅት ወቅት በጥራት ደረጃቸው እና በባህሪያቸዉ የሚለያዩ የአንድን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የአንድን የምርት ዘመን ከሌላ የምርት ዘመን እና የመኸር ምርትን ከበልግ ምርት ጋር ሳይቀላቀል ማዘጋጀት አለበት፡፡

## 11. <u>ስለማከማቻ መጋዘን አገልግሎት</u>

ማንኛውም የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ፡-

1/ ምርቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተመዘነ መሆኑን በማረጋገጥ መረከብ አለበት፡፡

2/ የአንድን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የአንድን የምርት ዘመን ከሌላ የምርት ዘመን እና የመኸር ምርትን ከበልግ ምርት ጋር ሳይቀላቀል ማከማቸት አለበት፡፡

3/ የማከማቻ መጋዘኑ ከምርቱ ጋር ተፃራሪ ከሆኑ እንደ ነዳጅ፣ ኬሚካሎች፣ ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ንክኪ የጸዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምርትን ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ማከማቸት የለበትም፡፡

## 12. <u>ስለሚዛን አገልግሎት</u>

1/ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ምርቱ በተመረተበት አካባቢ እንዲመዘን አመቺ በሆኑ አካባቢዎች የሚዛን አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ያመቻቻል፤ ምርቱ ከመኪና ላይ ሳይራገፍ የሚዛን አገልግሎት ይሰጣል፡፡

2/ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተመዘነ የምርት አይነት፣ መጠን፣ ዋጋ እና የተመረተበት ቦታ በአቅራቢ እና በላኪ ስም አደራጅቶ መረጃውን በሁለት የስራ ቀናት ዉስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

## 13. <u>ስለ ሽኝት አገልግሎት አሰጣጥ</u>

1/ በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል አቅራቢና ላኪ የቀጥታ ግብይት የፈጸሙባቸውን የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች በአካባቢው ወደሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ርክክብ ማዕከል የሽኝት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ርክክብ ማእከል የተመዘኑ የቅባት እህሎችን እና የጥራጥሬ ምርቶችን ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ፣ ማከማቻ መጋዘን ወይም ወደብ የሽኝት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## 14. <u>ስለቁጥጥር</u>

ሚኒስቴሩ፡-

1/ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች በሀገር ዉስጥ ከአለም አቀፍ የገበያ ዋጋ በላይ እንዳይገዙ እና በውጪ ገበያ ከአለም አቀፍ የገበያ ዋጋ በታች እንዳይሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

2/ ማንኛውም ላኪ የገዛውን፣ ወደ ዉጭ የላከውን እና በክምችት ያለውን የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፤

3/ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት መፈጸሙን ይቆጣጠራል፡፡

## 15. <u>ስለ ተከለከሉ ተግባራት</u>

የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም በቀጥታ ግብይት ሥርዓቱ ለሚሳተፍ ማንኛውም ሰው የተከለከለ ነው፡-

1/ ህገ ወጥ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት መፈጸም፤

2/ ውል ለገባለት ላኪ ግዴታውን ሳይወጣ ለሌላ ገዢ ሽያጭ መፈጸም፤

3/ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የርክክብ ማዕከል አቅርቦ ሳያስመዘን ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም ወደ ማከማቻ መጋዘን ማጓጓዝ፤

4/ ተገቢውን የመሸኛ ሰነድ ሳይዝ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የርክክብ ማዕከል፣ ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ፣ ወደ ማከማቻ መጋዘን ወይም ወደ ወደብ ማጓጓዝ፤

5/ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥም ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ምርቱ ከሚመረትበት አካባቢ ከሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የርክክብ ማዕከል ውጭ የምርት ሽኝት እና የምርት ሚዛን አገልግሎት መስጠት፤

6/ የአንድን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የአንድን የምርት ዘመን ከሌላ የምርት ዘመን ወይም የመኸር ምርትን ከበልግ ምርት ጋር ቀላቅሎ ማስመዘን፤ ማጓጓዝ፣ ማዘጋጀት ወይም ማከማቸት፤

7/ ለተፈጸመ ግብይት በወቅቱ ሙሉ ክፍያ አለመፈጸም፤

8/ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን የጥራት ደረጃ በሚጎዳ ሁኔታ ማጓጓዝ፣ ማዘጋጀት ወይም ማከማቸት፤

9/ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን ከተፈቀደለት የማከማቻ መጋዘን ውጪ ወይም ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ማከማቸት፤

10/ የቅባት እህሎች ወይም የጥራጥሬ ምርቶች የገበያ ዋጋ በመጠበቅ ማከማቸት፤

11/ከሚኒስቴሩ የኮንትራት ምዝገባ እና የኤክስፖርት የመላኪያ ፈቃድ ሳያገኝ የቅባት እህሎችን ወይም የጥራጥሬ ምርቶችን ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

12/ በተቆጣጣሪ ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት የሚጠየቀውን መረጃ ያለመስጠት ወይም የተጭበረበረና የተዛባ መረጃ መስጠት፡፡

16. <u>ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ከተመለከቱት የተከለከሉ ድርጊቶች አንዱን ፈጽሞ በተገኘ ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት ከቀጥታ ግብይት የማገድ፤ ወይም አግባብነት ባላቸው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለው) ድንጋጌዎች መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ የማገድ ወይም የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

17. <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት እና ውሳኔ አሰጣጥ</u>

1/ ማንኛዉም በቀጥታ ግብይት ሥርዓት የሚሳተፍ ሰው ወይም አስፈጻሚ አካል በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ካለዉ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ቅሬታውን በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ ቅሬታ የቀረበለት የሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3// የሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔዉን ካጸናዉ ቅሬታ አቅራቢዉ ጉዳዩን በ30 ተከታታይ ቀናት ዉስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

18. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ማናቸውም አካላት ይህንን መመሪያ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

19. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ህጎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም

20. <u>መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**መስከረም 2017 ዓ.ም**

**ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር**